# ቅንጅት ካናዳ የድጋፍ ቻፕተር
# *Kinijit Canada Support Chapter*

## <u>ተንጋለው ቢተፉ ተመልሶ ባፉ</u>

*ከቅንጅት ካናዳ የተሰጠ መግለጫ*
*አፕሪል 30 2007*

*የቅንጅት ዓለም አቀፍን እና የቅንጅት ሰሜን አሜሪካንን እንቅስቃሴ ለማሰናከል በእነሻለቃ ዮሴፍ ግዛው አማካኝነት እየተፈፀመ ያለው በጎ ያልሆነ እርምጃ ሁላችንንም እጅግ አሳዝኖናል። ድርጊቱ በማናቸውም መልኩ የቅንጅትን መሠረታዊ ዓላማ እና ራዕይ የሚፃረር ፣ ይልቁንም ለሕዝባዊ ድል መረጋገጥ የሕይወት እና የአካል መስዋዕት እየከፈሉ ባሉት መሪዎቻችን ብሎም ቅንጅት ፍቅር ነው ብለው አርማውን ባነገቡ ሚሊዮኖች ትግል ላይ እንደተቃጣ የጠላት በትር የሚቆጠር ነው።*

*ቅንጅት በፖለቲካ ረገድ ነፃ እና ፍትሐዊ ማህበረሰብ እንዲገነባ ፤ ሁሉም ዜጋ በሕግ ፊት እኩል መሆኑ በፅናት እንዲረጋገጥ ፤ መሪዎች ሃላፊነታቸውን በብቃት እና ግልፅ በሆነ የተጠያቂነት /transparency/ አግባብ እንዲያከናውኑ በአጠቃላይ የዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ በሕዝብ ሙሉ ተሳትፎ እንዲሠርፅ በመታገል ላይ ሃይል ነው።*

*የቅንጅት መርህ የፍቅር እና የመቻቻል ባህል እንዲዳብር የሚጋብዝ የሁሉም ዜጎች አለኝታ እንጂ ጥላቻ እና መከፋፈልን የሚያራምድ የጥቂቶች ሴራ መጎንጎኛ መድረክ አይደለም። የቅንጅት ራዕይ በመሪዎቻችን አርቆ አስተዋይነት እና እየከፈሉት ባለው ታላቅ መስዋዕትነት ጎልብቶ በመላ ዜጎች ዘንድ ታላቅ ክብርን ተጎናፅፏል።*

*ቅንጅት ያነገበውን ታሪካዊ እና ግዙፍ ህዝባዊ ተልዕኮ ዳር ለማድረስ ሁለንተናዊ ዝግጁነት እና ብቃት ልንገነባ ይገባል። በመሆኑም ዛሬ በወያኔ ማጎሪያ ፍዳቸውን እየቆጠሩ ያሉት መሪዎቻችን እነርሱ የዘሩትን የፍቅር እና "ከምንም ነገር በላይ ኢትዮጵያዊነት" የሚለውን አርማ በፅናት ማራመድ ይጠበቅብናል። መሪዎቻችን ከግል ጥቅም እና ምቾት ወይም ከጊዜያዊ የግርግር ፓርላማ ወንበር ይልቅ የአገር ዘላቂ ህልውና እና ታሪካዊ ክብር ይበልጣል ብለው በቁርጠኝነት መቆማቸው ለላቀ ሃላፊነት ሊያዘጋጀን ይገባል።*

*መሪዎቻችን በማያወላውል ሕዝባዊ ፍቅር መልሰው ያቀጣጠሉትን የአንድነት ፣ የሰላም ፣ የነፃነት እና የዕድገት ትግል እርምጃው ሳይሰናከል ወደ ላቀ እርከን ለማድረስ በተወሰነ ደረጃ ሃላፊነቱ የወደቀው በውጭ አገር ነዋሪ በሆንነው ኢትዮጵያውያን ተከሻ ላይ መሆኑ ለጠላትም ለወዳጅም ግልፅ ነው። በአመራር ረገድ ይህን ሃላፊነት በተገቢው መንገድ መወጣት እንዳይቻል እነሻለቃ ዮሴፍ እየፈጠሩ ያሉት መሰናክል ግን በቀላሉ የሚታይ አይደለም ።*

*የቅንጅትን ዓላማ አንግቤ አገሬን ከጥፋት እታደጋለሁ የሚል ኢትዮጵያዊ ከመሪዎቹ የሚጠብቀው አሉባልታን ማናፈስ ፣ ግለሰቦች ላይ ያነጣጠረ ሴራ እና ሥም ማጥፋት ላይ መሠማራት አለመሆኑን በተለያየ መድረክ በውል ሰናስታውቅ ብንቆይም እነሻለቃ ሊያዳምጡን አልፈቀዱም። ይባስ ብሎ የቅንጅት አለም አቀፍን እና የሰሜን አሜሪካውን አመራር በሕግ ሽፋን ለማዳከም ተነስተዋል።*

*ይህን በሚመለከት ዓለም አቀፍ የቅንጅት አመራር ያሳየውን ብስለት የተመላበት ትዕግስት ብሎም ጉዳዩ የውስጥ ችግር እንደመሆኑ አደባባይ ወጥቶ መነታረኩ አላስፈላጊ ብቻ ሳይሆን ጎጂ መሆኑን አበክሮ መወትወቱ ሊደነቅ የሚገባው እርምጃ ነው እንላለን። አሁንም ቢሆን ይህን አቋሙን እስከዘለቄታው እንዲየራምድ ብሎም በእስር እየተንገላቱ ክቡር መስዋዕት በመክፈል ላይ ያሉ መሪዎቻችን ለሕዝባችን የገቡትን የማይታጠፍ ቃልኪዳን በፅናት መጠበቅ እንዲችል ለዚህም ያላሰለሰ ድጋፋችን እንደማይለየው ልናረጋግጥ እንወዳለን።*

*ሁሉም ዜጋ የሚመኘው ነገር ቢኖር ወያኔ/ኢህዴግ የዘረጋው ዘረኛ የአፈና ሥርዓት ተወግዶ ዲሞክራሲያዊ ስርዓት እንዲያብብ ለማስቻል መሆኑን ላንድ አፍታ እንኳን መዘንጋት የለብንም። በአንድነት መቆማችን በራሱ የጠላትን ሠፈር ምን ያህል እንደሚያሽብር የምርጫ 97 ዋዜማ የድጋፍ ሰልፍ ለጥቆም በምርጫው የተገኘው ሕዝባዊ ድል ያረጋገጡት ታሪካዊ ሃቅ ነው ብለን እናምናለን። መላ ሃይላችን የዲሞክራሲን ፈር በቀደደው በዚህ ሕዝባዊ ትግል ጥንካሬ ላይ ማተኮሩ ቀርቶ ውሱን በሆኑ ግላዊ ጉደዮች ላይ የምንጠመድ ከሆነ በእስር የሚንገላቱት መሪዎቻችን የገቡትን ቃልኪዳን እንደመርገጥ ፣ የሕዝብን አደራ ያለምንም ይሉኝታ እንደመብላት ይቆጠራል። እግር የወጋ እሾህ ሥራ ማስፈታቱ አይቀርም እንዲሉ የትግሉን ግሥጋሤ ለማደናቀፍ በማናቸውም መልኩ የሚከሰት ችግር አሉታዊ ተፅእኖ እንደሚኖረው የሚታወቅ ጉዳይ ነው። ቆሜለታለሁ የሚሉትን አላማ በአደባባይ ማሳደድ ተንጋሎ የመትፋትህን ያህል መዘዙ ለራሰም የሚበጅ አይሆንም።*

*በመሆኑም እነ ሻለቃ ከዚህ አስተዋይነት የጎደለው አድራጎታቸው ተቆጥበው ከቅንጅት አለም አቀፍ አመርር ጋር ግልፅ እና ገንቢ ውይይት እንዲያደርጉ በድጋሚ እያሳሰብን ቅንጅት ፍቅር ነው እያልን ጥላቻ ፤ ቅንጅት አንድነት ነው እያልን መከፋፈል ፤ ቅንጅት ግልፅነት ነው እያልን ድብቅ ሴራ ፤ ቅንጅት ዲሞክራሲያዊ ነው እያልን አምባገነንነት መገንባት የሚታሰብ ጉዳይ አለመሆኑ በውል ሊጤን እንደሚገባው በአፅንዖት እንገልፃለን።*

***የተባበረ ሰላማዊ ሕዝባዊ ትግል ያሸንፋል!!!***

*<u>የቅንጅት ካናዳ ድጋፍ ድርጅት አባል ቻፕተሮች</u>*

*በቶሮንቶ የቅንጅት ድጋፍ ቻፕተር ፤*
*በዊኒፔግ የቅንጅት ድጋፍ ቻፕተር ፤*
*በካልጋሪ የቅንጅት ድጋፍ ቻፕተር ፤*
*በቫንኮቨር የቅንጅት ድጋፍ ቻፕተር ፤*
*በዋተርሉ የቅንጅት ድጋፍ ቻፕተር*